www.chilot.me

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግሥት

# አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ

www.chilot.me

# ማውጫ


ገጽ

1. መግለጫ........................................................................ 1

2. የትምህርት ዓላማዎች................................................... 4

    2.1 አጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎች........................... 4
    2.2 ዝርዝር የትምህርት ዓላማዎች.............................. 5

3. የትምህርት ሥልቶች...................................................... 7

    3.1 ሥትዓተ ትምህርት................................................ 7
    3.2 የትምህርት እርከን................................................ 8
    3.3 የትምህርት ምዘና................................................. 10
    3.4 የመምህራን ጉዳይ............................................... 11
    3.5 ቋንቋና ትምህርት................................................ 12
    3.6 የትምህርት፣ የሥልጠና፣ የምርምርና የልማት ተስተጋብሮት...13
    3.7 የትምህርት ድጋፍ ሰጪዎች.................................. 14
    3.8 የትምህርት አደረጃጀትና አመራር........................... 15
    3.9 የትምህርት ፋይናንስ........................................... 16

4. ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች........................... 17

## 1. መግለጫ

ትምህርት የሰው ልጅ በኑሮ ትግሉ ያከማቻቸውን ግኝቶችንና ተሞክሮዎችን ማስተላለፊያና አዲስ ግኝቶችን ማፍለቂያ ሂደት ነው። ትምህርት ግለሰቦችን በእውቀት፣ በግንዛንቤ፣ በአስተሳሰብ፣ በአመለካከት፣በሥነ-ውበትና በእሴት እንዲሁም በችሎታና በክህሎት በማነጽ ለራሳቸውና ለኀብረተሰብ ሁለንተናዊ እድገት ፍሬያማ ተሳትፎ ለማድረግ ያስችላቸዋል። የትምህርት ሂደት በግለሰብና በኀብረተሰብ ተስተጋብሮት ለአጠቃላይ ኀብረተሰብ ህልውናና እድገት ቁልፍ ሚና አለው። ስለሆነም በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል።

የትምህርት አንዱ ባሕርይ መሠረታዊ እውቀት በማስጨበጥ፣ በግለሰብም ሆነ በኀብረተሰብ የችግር ፈቺነት አቅምን፣ ችሎታን ባህልን ማጎልበት ነው። በመሆኑም ትምህርት ጎጂ ባህሎችን በመለየትና በማስወገድ፣ ጠቃሚና አዲስ ባህሎችን በመቅሰምና በማዳበር፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በኀብረተሰቡ በማስረጽ፣ የሰው ልጅ አካባቢውን እንዳስፈላጊነቱ አሻሽሎና ለውጦ በሚገባ ተንከባክቦና አልምቶ ለሁለንተናዊ እድገቱ እንዲያውለው ይረዳዋል። ከዚህ ጋር ነፃነት፣ መብትና ግዴታ ማኀበራዊ ለሰብአዊ መብቶች መከበርና እኩልነትና መግባባት እንዲኖር በአጠቃላዩም ለሰብአዊ መብቶች መከበርና መስፈን ትምህርት የበኩሉን ሚና ማሟላት ይኖርበታል።

ትምህርት ብቻውን ተነጥሎ የሚከናወን ሳይሆን ከምርምር ከሙያዊ ተግባርና ከልማት ጋር ተስተጋብሮ ለኀብረተሰቡ ሁለንተናዊ እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለበት።

የሀገራችን ትምህርት ሁኔታ በዓላማ በይዘት በአቀራረብ በሥርጭት በግባትና በሂደት እንዲሁም በውጤት ሲታይ ተማሪዎች ተገቢውን ትምህርት ቀስመው የችግር ፈቺነት ባሕርይንና ችሎታን እንዲያጎለብት አስችሎአቸዋል ለማለት አያስደፍርም። የሕዝብ ኑሮ ለማሻሻል ተገቢውን ባህል በማዳበር ሳይንስና ቴክኖሎጂን በፀብረተሰቡ አስርጾ አካባቢያቸውን ለመንከባከብ ለማልማትና ማኀበር-ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎአቸውን ለማጠናከር እንዲያስችላቸው ያደረገው አስተዋጽኦ ጎልቶ አልታየም።

በሥርጭቱም ረገድ ዕድሜአቸው ለትምህርት ከደረሱት መካከል በተለይ በአንደኛ ደረጃ የሚሳተፉት ከ22 በመቶ በታች ሲሆኑ፣ ከነዚህም ከዝቅተኛ ክፍል አቋርጠው ወደ ማይምነት የሚመለሱት በርካታ ናቸው። በክልሎች መካከል ያለው ተሳትፎ ሲታይም ሥርጭቱ ፍትሃዊ አይደለም። በአጠቃላጥ ሰፊ የማይምነት ችግር መኖሩ በግልጽ ይታያል። የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ችግሮችም እንደዚሁ የጎሉ መሆናቸው ይታወቃል። በተለይ በእነዚህ ደረጃዎች የትምህርት ተገቢነትና ጥራት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ይገኛል በከፍተኛ ትምህርት በሳል ችግር ፈቺ ምሁራንን በማፍራትም ሆነ ለሕዝብ ጥቅምና ለሀገር እድገት የሚጠበቀውን ያክል የጥናትም ሆነ የምርምር ውጤት ጎልቶ አልታየም።

እነዚህ ድክመቶች ባመዛኙ የሚመነጩት ከሥርዓት ትምህርቱ፣ ከትምህርቱ አሰቀጥና ካቀራረቡ እንዲሁም ለትምህርቱ ከሚያስፈልገው ግባት ባጠቃላይም የትምህርቱን ሁሉ አቀፍ ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ፖሊሲ ባለመኖሩ ነው። ይህ ደግሞ

www.chilot.me

እንደሌሎች የልማትና የማኅበራዊ ችግሮች መንስኤዎች ባመዛኙ የነበሩት ሥርዓቶች መሆናቸው ይታወቃል፡፡

የቀድሞ ሥርዓት የዘላለማዊነት ሽፋን የለበሰ ሊለወጥ የማይቻል ሆኖ ይቀርብ ስለነበረ የትምህርትን የፈጠራንና የችግር ፈቺነትን ሚና አደብዝዞ ዞት ቆይቷል፡፡ ሥርዓቱ ሥልጣንና ጥቅምን ለጥቂቶች በግል ባለቤትነት የሰጠና ችግር የበዛበት እንደነበር ይታወቃል፡፡ በዚህ ውጥረት ይሰጥ የነበረው ትምህርት ሥርጭቱ ውሱን ከመሆኑም በላይ ባስተዳደር ዝርዝር ፈጻሚነትና ባገልግሎት አቅራቢነት እንዲሁም ሳይሠሩ የመጠቀም ፍላጎትንና አመለካከት በማስረጽ ላይ ያተኮረ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

በወታደራዊ መንግሥት ዘመን ምንም እንኳን በሕዝብ በኩል ከፍተኛ የትምህርት ፍላጎት ግፊት የነበረ ቢሆንም ከጦርነት ተርፎ ለዘርፉ ለማደራ ይችል የነበረው ገንዘብና ሌሎች ግባቶች በጣም አናሳ ነበሩ፡፡ አገዛዙ ከአጼዎቹ የበለጠ አምባገነን ስለነበረም ቀደም ብለው የነበሩት ደካማ ባሕሪያት ተባብሰው ቀጠሉ፡፡ ማይምነት በሰፈነባት አገራችን የተማሪ-ሥራ-አጥ እየጨመረ መምጣት የኅብረተሰቡን ችግር አባብሶታል በሥራ ላይ በተሠማራውም ዘንድ ተገቢው እውቀት ችሎታ ክህሎትና የሥራ ጽናት ሰርጾታል ለማለት ያስቸግራል፡፡

የትምህርት ችግሮች መንስኤዎች ከሌሉች ሁኔታዎች ጋር ተዳምረው በአገራችን ትክክለኛ የትምህርት ፖሊሲ አለመኖር ትምህርት በዓላማው በይዘቱ በማስተማር መማር ሥነ-ዘዴው በሥርጭቱ በአደረጃጀቱ በአስተዳደሩ በፋይናንስ በምርምሩ በድጋፍ ሰጪዎች ወዘተ ብቃት ማጣት ናቸው፡፡

ይህንን ሁኔታ ለመለወጥ ተስማሚ የትምህርት ፖሊሲ ማስፈለጉ አያጠያይቅም በመሆኑም አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተዘጋጅቷል

ፖሊሲው ከሕፃናት አስተዳደግ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ ልዩ ትምህርትን ጨምሮ ያለውን መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን እንዲሁም ሥልቶችንና ተግባሮችን አጠቃልሉ በሚያሳይ መልኩ ተቀርጿል፡፡

ትምህርት የችግር ፈቺነትን አቅምና ባህል ለማጎልበት እንዲያስችል የትምህርት ይዘት የሥርዓተ ትምህርት አወቃቀር የትምህርት አቀራረብ የትምህርት ቅስሞሽ ሳይንሳዊና ተግባራዊ እንዲሆን ያስገነዝባል፡፡

ከዚህ ጋር በማያያዝ ትምህርት ምርምርና ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች የልማት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች አስተዋጽኦ ተገቢው ተስተጋብሮት እንዲኖራቸው ፈር ያስይዛል፡፡

የትምህርት እርከንን ከተማሪው የባሕርይ ገጽታዎች ጋር አገናዝቦ ይገልጻል፡፡ ትምህርትና ሥልጠና የሚያስገኙዋቸው የባሕርይ ለውጦችና ውጤቶችን ለመገምገም የትምህርት ምዘና ምን መሆን እንዲኖርበት ያመለክታል፡፡ በትምህርትና በማስተማሪያ ቋንቋ ረገድም ሲሆን የሚገባውንና የሚቻለውን ያስቀምጣል፡፡ እንዲሁም የመምህርነት ሙያ በመማር ማስተማር ሂደት ትውልድን በእውቀት በአስተሳሰብ በችሎታና በክህሎት የመቅረጽ ኃላፊነት ያለበት እንደመሆኑ ለማሠልጠኛ ተቋሞች አደረጃጀት ለሠልጣኞች

ምልመላ ለሥልጠና መርሐ ግብሮችና ሥነ-ዘዴዎች ለመምህራን መራሔ ሙያ ለሥራ ለእድገትና ለኑሮ ሁኔታ የሚሰጠውን ትኩረት ይገልጻል፡፡

ለመማር ማስተማር ሂደት መጠናከርና መስፋፋት የትምህርት መሣሪያዎች የትምህርት ቴክኖሎጂና የትምህርት ፋሲሊቲ በተገቢው ሁኔታ መቅረባቸውና ለተፈላጊው ተግባር በትክክል መዋላቸው የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ይጠቁማል አመቺ የትምህርት አካባቢ መፈጠር እንደሚኖርበት የትምህርት አደረጃጀትና አመራርም ዲሞክራሲያዊና ሙያዊ ሆኖ ቀልጣፋና ቀና በሁሉም አቅጣጫ ቅንጅት ባለውና ባልተማከለ አሠራር ተገቢውን ውጤት የሚያስገኝ እንዲሆን ያስገነዝባል፡፡

የትምህርት ፋይናንስና ምንጭ አደላደሉና አጠቃቀሙ ትምህርትን በጥራትና በስፋት ለማዳረስ የሚያስችል እንዲሆንና ፍትሃዊ ቀልጣፋ ቀናና ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ አሠራር የሚፈጠርበትን ሥርዓት ይጠቁማል፡፡

ስለሆነም የሀገርና የሕዝብ ችግሮችን ለመፍታት የተዘጋጀና ሰብአዊና አገራዊ ኃላፊነት የሚሰማው ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ አመለካከቱ የተስተካከለ ከተፈጥሮ ተጽእና በተግባር ለመላቀቅ የተዘጋጀ የማምረትና የመመራመር አቅሙ የዳበር ዜጋ ለማዘጋጀት የሚያስችል አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ቀርቧል፡፡

## 2. የትምህርት ዓላማዎች

### 2.1. አጠቃላይ ዓላማዎች

2.1.1. ትምህርትን በማስፋፋት በተለይም መሠረታዊ ትምህርትን ለሁሉም በማዳረስ የግለሰብን የአካልና የአእምሮ ተሰጥኦ በመጎልበት የሚያጋጥሙ ችግሮችን የማወቅና የመፍታት ዝንባሌና ችሎታ ያዳበሩ ዜጎች ማፍራት

2.1.2. የትምህርትን ግለሰባዊና ማኀበራዊ ጠቀሜታ ለማሳደግ ትምህርትን የምርት መሣሪያ ምርትንም የትምህርት መሣሪያ በማድረግ ሀብትን የሚንከባከቡና በተገቢው መንገድ የሚጠቀሙ በልዩ ልዩ ተክህኖ የሠለጠኑ ዜጎች ማፍራት

2.1.3. የማኀበራዊ ኑሮና ግንኙነት ባህልን በማበልጸግ ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብሩ ለሰው ልጅ ደህንነትና እኩልነት ለፍትሕና ለሠላም የቆሙ በሥነ-ምግባርና በዲሞክራሲ ባህል የታነጹ ለሕዝብና ለሀገር ፍቅር ያላቸው ሁለንተናዊ ሰብእናቸው የተሟላ ዜጎችን ማፍራት

2.1.4. የማመዛዘን የመፍጠርና የመመራመር ችሎታን በማዳበር ጎጂ ባህሎችን ከጠቃሚዎቹ የሚለዩ እውነትን የሚሹ ለእውነት የሚቆሙ ውበትን የሚያደንቁ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት መስረጽና ማደግ አዎንታዊ አመለካከት የሚያሳዩና አስተዋጽኦ ያላቸው ዜጎች ማፍራት

www.chilot.me

2.1.5. ትምህርትን ለአካባቢው ተስማሚና ተገቢ በማድረግ አካባቢያቸውን የማወቅ የማጤንና የመገንዘብ የመመዘንና የመገምገም የመተንተንና የመለወጥ የማድነቅ ችሎታ ያላቸው ዜጎች ማፍራት

## 2.2. ዝርዝር ዓላማዎች

2.2.1. መደበኛና መደበኛ ባልሆነ መርሐ ግብር ተገቢና ተስማሚ የትምህርትና የሥልጠና ሥርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ

2.2.2. በትምህርት ሂደት የተማሪዎችን የመፍጠርና የመመራመር ችሎታን ማጎልበት ሥነ-ውበትንም የማድነቅና የመፍጠር ብቃት ማዳበር

2.2.3. የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ማለትም ለየት ያለ የትምህርት አቀራረብ የሚያስፈልጋቸው እንደየችሎታቸውና ፍላጎታቸው እንዲማሩ ማድረግ

2.2.4. መሠረታዊ እውቀቶችን ከልዩ ልዩ ሥልጠናዎች ጋር በየደረጃው አቀናጅቶ መስጠት

2.2.5. በልዩ ልዩ ተክህኖ ሰዎችን በማሠልጠን የአራቱን የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ማርካት

2.2.6. ለጥናትና ምርምር ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ትምህርት ሥልጠናና ምርምር ከልማት ጋር ተገቢው ተስተጋብሮት እንዲኖራቸው በቅንጅት ማካሄድ

2.2.7. ትምህርት ሴኩላር ሆኖ እንዲካሄድ ማድረግ

2.2.8. ትምህርት ባህላዊ ቴክኖሎጂን ለማሳደግና ተስማሚ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚረዳ መሣሪያ እንዲሆን ማድረግ

2.2.9. የዲሞክራሲ ባህል የሚያሰፍን የመቻቻል ቅራኔን በሠላምና በውይይት የማርገብና የመፍታት እንዲሁም ማኅበራዊ ኃላፊነትን የመወጣት ግንዛቤን ከፍ የሚያደርግ ትምህርት መስጠት

2.2.10. ለእኩልነት ለነፃነት ለፍትሕና ለዲሞክራሲያዊ አንድነት የቆሙ በሥነ-ምግባር የታነጹ ዜጎችን ማፍራት የሚያስችል ትምህርት መስጠት

2.2.11. የሥራ ክቡርነት ባህልና ልምድ እንዲጎለብትና ለሥራ ከፍተኛ ቦታና ክብር እንዲሰጠው የሚያደርግ ትምህርት መስጠት

2.2.12. ብሔር/ብሔረሰቦችን በራሳቸው ቋንቋ እንዲማሩ ማድረግ እንዲሁም ለጋራ ግንኙነት እንዲረዳ አንደ አገር አቀፍና አንድ ዓለም አቀፍ ቋንቋዎችን ማስተማር

2.2.13. ትምህርት በሁሉም መልኩ ስለሴቶች ሚናና አስተዋጽኦ ያለውን ማኅበራዊ አመለካከት የሚለውጥና ትክክለኛውን ግንዛቤ የሚያንፀባርቅ ማድረግ

2.2.14. የተፈጥሮ ሀብትና የሀገር ታሪካዊ ቅርስን የሚንከባከቡ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ አመለካከት ያላቸው ዜጎችን ማፍራት የሚያስችል ትምህርት መስጠት

2.2.15. የግለሰብንም ሆነ የኅብረተሰብን ንብረት በተገቢው መንገድ የመጠቀምና የመጠበቅ አመለካከትና ችሎታን ያዳበሩ ዜጎችን ለማፍራት የሚያስችል ትምህርት መስጠት

## 3. የትምህርት ሥልቶች

### 3.1. ሥርዓተ ትምህርት

3.1.1. ሥርዓተ ትምህርት በሀገሪቱ የትምህርት ዓላማዎች ላይ ተመሥርቶና አስፈላጊውን ደረጃ ጠብቆ በየትምህርት እርከኑ ተገቢውን የማሪ የባሕርይ ገጽታ ሊቀረጽ በሚያስችል ሁኔታ መዘጋጀቱ ይረጋገጣል

3.1.2. ሥርዓተ ትምህርት ሲዘጋጅም ሆነ ሲተገበርና ሲገመገም ኅብረተሰቡ በሰፊው የሚሳተፍበት ሥርዓት በመቀየስ በየደረጃው የትምህርት ባለሙያዎችን በምህራንን ቁልፍ የሆኑ የልማትና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶተንና የምርምር ተቋሞችን እንዲሁም ተጠቃሚ ኅብረተሰቡን ባቀፈ ሁኔታ ይከናወናል

3.1.3. በማዕከልና በክልል የሚካሄድ የሥርዓተ ትምህርትና የመጻሕፍት ዝግጅት በመሠረታዊ ሥነ ትምህርትና ሥነ አእምሮ መርሆዎች ላይ ተመሥርቶ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን አገናዝቦ ሀገር አቀፍና አካባቢያዊ ጭብጦችንና ፍላጎቶችን አካቶ ለጾታ ጉዳዮችም ትኩረት በመስጠት ይከናወናል

3.1.4. ሥርዓተ ትምህርቱ በየደረጃው በትምህርት እርከኖች መካከል ተገቢው መወራረስና መደጋገፍ ኖሮ አስፈላጊው የደረጃ ተመጣጣኝነት /ስታንዳርድ/ ስለመጠበቁ ትምህርትና ሥልጠና በኅብረተሰቡ ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ ከምርምርና ከልማት ጋር በትክክል ተስተጋብሮ ተገቢውን ውጤት ስለማግኘቱ ተከታታይና ወቅታዊ ግምገማ የሚካሄድበት ሥልት ሊፈጠር ይገባል ለዚህም ተጠናክረው እንዲሠሩና ከሌሎች የልማት መሥሪያ ቤቶች ድርጅቶችና የምርምር

www.chilot.me

ተቋሞች ጋር አስፈላጊውን የሥራ መደጋገፍና የአሠራር ቅንጅት እንዲኖር ይደረጋል

## 3.2. የትምህርት እርከን

3.2.1. በአፀደ ሕፃናትና በተመሳሳይ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ሕፃናትን ለተስተካከለ የአካልና የአእምሮ የስሜትና የማኅበራዊ ግንኙነት እድገትና ለመደበኛ ትምህርት የሚያመቻች ይሆናል

3.2.2. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በስምንት ዓመት የሚጠናቀቅ ሆኖ በመሠረታዊና አጠቃላይ ትምህርት ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የሚያዘጋጅና በሂደት የሚዳብር መሠረታዊ ችሎታ ያላቸውን ዜጎች የሚያፈራ ይሆናል

3.2.3. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል ተከፍሎ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያ ሳይክል /9ኛና 10ኛ/ የሚሰጠው አጠቃላይ ትምህርት ተማሪዎች ተሰጥኦዋአቸውን ችሎታቸውን መርምረው የሚስማማቸውን የሙያ ዘርፍ ለመምረጥና ለቀጣዩ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም በመጠነኛ ሥልጠና ወደ ምርት ተግባር ለመግባት የሚያስችላቸው ሆኖ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ይሆናል፡፡ በሁለተኛው ሳይክል /11ኛና 12ኛ/ የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎችን ከአጠቃላይ ትምህርት ጋር አዛምዶ በሠለጠኑበት የሙያ ዘርፍ በቂ ችሎታና ክህሎቶች ኖሯቸው በእርሻ ቴክኖሎጂ በኑሮ ዘዴ ሳይንስና በንግደ ሥራ በመሳሰሉት መሥራት የሚችሉትና ለከፍተኛ ትምህርት በብቃት የተዘጋጁ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

3.2.4. በዲኘሎም በመጀመሪያ ዲግሪና በድኅረ ምርቃ የከፍተኛ ትምህርት መርሐ ግብሮች የሚሰጠው የትምህርት ቅንብር ሂደትና ሥልጠና ምርምርን ምርትንና አገልግሎትን አቀናጅቶ በየትኩረት መስኩ በተመራማሪነት በሙያ መሪነትና በአዲስ እውቀት አድማስ አስፊነት ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን ችግር ፈቺ ምሁራንን የሚያፈልቅ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

3.2.5. ከመደበኛ ትምህርቱ አኳያ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ከመሠረታዊ ትምህርት ጀምሮ በየደረጃው ይሰጣል፡፡

3.2.6. ከመሠረታዊ ትምህርት ቋንቋን ስሌትን የአካባቢና የቤተሰብ ኑሮ ትምህርትን ግብርናን እደ ጥበብን ኑሮ ዘዴን የጤናን የአገልግሎትና የሲቪክ ትምህርትን አጠቃሎ ይሰጣል፡፡

3.2.7. በየደረጃው የሚሰጠው መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በይዘቱ ተጨባጭ ያካባቢን የኑሮና የማኅበራዊ ችግር ፈቺነት በሕሪንና ችሎታን

የሚያጎለብት ሆኖ ተመጣጣኝነቱ የመደበኛውን ትምህርት የእርከን የባሕርይ ገጽታ የሚያሟላ ይሆናል፡፡

3.2.8. ከአጠቃላይ ትምህርት መርሐ ግብር አኳያ ከመሠረታዊ ትምህርት ጀምሮ ከየሳይክሉ ለሚወጡ ተማሪዎች በአገሪቱ የተለያዩ የኢኮኖሚና የሰው ኃይል ፍላጎቶች ላይ ተመሥርቶ በመነሻ /በጀማሪ/ በመለስተኛና መካከለኛ ባለሙየነት ለልዩ ልዩ ተቀጣሪነትና ለራስ አገዝ ሥራዎች የሚዘጋጁ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ የቴክኒክና ሙና ሥልጠናዎች ጾታ ሳይለጥ ይሰጣል፡፡

ከመጀመሪያ ደረጃ አቋርጠው ለሚወጡ ዕድሜያቸው ለሚፈቅድላቸው /በጀማሪ/ በመነሻ ባለሙያነት በግብርና በእደ ጥበብና በኮንስትራክሽን በመሠረታዊ የመዝገብ አያያዝ በአኻሬንቲስሽኘ ለምርትና ለሥራ ሥምሪት የሚያበቁ ልዩ ልዩ ሥልጠና ኘሮግራሞች ይዘረጋሉ

ከመጀመሪያው ደረጃ በኃላ በመለስተኛ ባለሙያነት በግብርና በኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂ በኮንስትራክሽን በንግድ ሥራና በኑሮ ዘዴ ለሥራ ፈጣሪነትና /ኢንተረኘረነርሽኘ/ ለተቀጣሪነት የሚያበቁ የሥልጠና ኘሮግራሞች ይቀረጻሉ፡፡

ከሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል በኃላ በመካከለኛ ባለሙያነት በኢንዱስትሪያል ቴክኖሎጂ በግብርና በንግድ ሥራ በኮንስትራክሽን በኑሮ ዘዴ ለሥራ ፈጣሪነትና ለተቀጣሪነት የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍሪያ የሥልጠና ኘሮግራሞች ይደራጃሉ

3.2.9. ለአካል ጉዳተኞችና ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው በየደረጃው የልዩ ትምህርት መርሐ ግብሮች ይዘጋጃሉ

## 3.3. የትምህርት ምዘና

3.3.1. ተማዎች በየክፍሉና በየደረጃው የሚሰጠውን ትምህርትና ሥልጠና የሚገባ ያጠናቀቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በአጠቃላይ በቀለምና በተግባራዊ ትምህርት ተከታታይ ምዘና ይኖራል፡፡

3.3.2. በስምንተኛና በአሥረኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ላይ የአጠቃላይ የቀለምና ተግባራዊ ትምህርቶችን ያካተተ አገር አቀፍ /ብሔራዊ/ ምዘና ይኖራል፡፡

3.3.3. ከአንድ ደረጃ ወደሚቀጥለው ደረጃ ለመሸጋገር ተማሪዎች ከተማሩት ውስጥ ቢያንስ ሃምሳ መቶ የሚሆነውን በእውቀት በችሎታና በክህሎት ጨብጠው መገኘታቸው ይረጋገጣል

3.3.4. ተማሪዎች በመረጡት የሙያና የቀለም ዘርፍ የሚሰጠውን ትምህርትና ሥልጠና ለማጠናቀቃቸውና ወደሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ መሸጋገር ለመቻላቸውና እንዲሁም በሠለጠኑበት የሙያና የቀለም ዘርፍ ወደ ሥራ ዓለም ለማሠማራት የተዘጋጁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት /ሰርተፊኬት/ አግባብ ያለው ተቋም ይሰጣል።

3.3.5. ከአጠቃላይ ትምህርት አኳያ በመነሻ /በጀማሪ/ በለስተኛና በመካከለኛ ባለሙያነት በሠለጠኑበት የሙያ ደረጃ ተከታታይና የማጠቃለያ ተግባራዊ ምዘና በመስጠት ሠልጠኞች የብቃት ምስክር ወረቀት ያገኛሉ።

3.3.6. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ወደልዩ ሥልጠናዎች መግባት ለሚፈልጉ ተማሪዎች በሚመርጡት የሙያ ዘርፍ ተቀባይ ተቋም የሚያወጣቸውን የመግቢያ መሥፈርቶች ማለፍ ይኖርባቸዋል።

3.3.7. ብሔራዊ ፈተናዎችን ለመምራትና በጠቅላላ ስለትምህርትና ሥልጠና ምዘናና ፈተና ሳይንሳዊ አመራር ለመስጠት አስፈላጊውን የሠለጠነ የሰው ኃይል በጀት ቁሳቁስ የሚያደራጅ ራሱን የቻለ ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር የሆነ የብሔራዊ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ድርጅት ይቋቋማል።

3.4. የመምህራን ጉዳይ

3.4.1. ለየእርከኑ ሥልጠና የሚመለመሉ እጩ መምህራን በችሎታቸው በታታሪነታቸው እንዳግባቡ በአካል ብቃታቸው በአእምሮ ጤንነታቸውና ለሙያው ባላቸው ዝንባሌ መሆኑ ይረጋገጣል።

3.4.2. የእጩ መምህራን የምልመላ ሥርዓት በአሠልጣኝ ተቋሞች በቀጣሪ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበር የጋራ ኃላፊነት የሚዘጋጅበት ሁኔታ ይመቻቻል።

3.4.3. የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና የሠልጣኞች ጠቅላላ እውቀት የአስተሳሰብ ለውጥ የሙያ ሥነ ምግባርና ተግባራዊ ችሎታን በሚያጎለብት ሁኔታ መካሄዱ ይረጋገጣል።

3.4.4. የመምህራን ትምህርትና ደረጃው በመምህርነት በማስተማር ተግባር ከመሠማራታቸው በፊት ለየትምህርት ደረጃው በብቃት ስለመሠልጠናቸው ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

3.4.5. ከአፀደ ሕፃናት እስከ ከፍተኛ ትምህርት የሚሠማሩበትና የተሠማሩበት መምህራን በቅድመ መምህርነት ሥልጠናና ተከታታይ

ሥልጠና በሙያውና በማስተተማሪያ ቋንቋ ብቃት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

3.4.6. ለመምህራን ሙያዊ እድገት መሠረቱ ከሥራ ውጤትና መራሔሙያ ጋር ተገናዝቦ ተከታታይ ትምህርትና ሥልጠና ይሆናል፡፡

3.4.7. በትምህርት ደረጃቸው በችሎታቸው በሥራ አፈጻጸምና በምርምር ሥራ ውጤታቸው በሥነ ምግባራቸውና በተመሳሳይ መሥፈርቶች እየተገመገሙ በሙያቸውና በደረጃቸው እንዲያድጉ የሚያስችል ሙያዊ የእድገት መሰላል ይዘጋጃል፡፡

3.4.8. የየደረጃው የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋሞች የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞችን ጨምሮ ተገቢው ሥልጣን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ኖሯቸው ራሳቸውን ችለው ተግባራቸውን በብቃት እንዲያካሂዱ ይደረጋል፡፡

3.4.9. የመምህራን ትምህርትና ሥልጠና ተቋሞች መርሐ ግብሮቻቸውን ከሚያሠለጥኑበት የትምህርት እርከን ፍላጎት ጋር አጣጥመው ማዘጋጀታቸውና መተግበራቸውና መተግበራቸው ይረጋገጣል፡፡

3.4.10. በመምህራን ምልመላ ሥልጠናና በሥራ ሥምሪት ወቅት ለሴቶች ተሳትፎ ልዩ ትኩረት ስለመስጠቱ ይረጋገጣል፡፡

3.4.11. የልዩ ትምህርት መምህራን ሥልጠና መርሐ ግብሮች በየደረጃው ለሌሎች መርሐ ግብሮች በተቋቋሙ የማሠልጠኛ ተቋሞች ውስጥ እንደአስፈላጊነታቸው በቅንጅት ወይም በመዋሐድ እንዲካሄዱ ይደረጋል፡፡

3.4.12. የመምህርነት የሥራ ባሕርይ የተለየ ፍላጎትን ጥረትንና ችሎታን ስለሚጠይቅ በመምህርነት ሥራ የሚሠማሩትን በሥራቸው ላይ ለማነቃቃትና ለኑሮ አመቺ ባልሆነ አካባቢዎችም የሚሠማሩትን ለማበረታታት ልዩ ልዩ የማነቃቂያ ሥልቶች እንዲቀየሱ ይደረጋል፡፡

## 3.5. ቋንቋና ትምህርት

3.5.1. በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማር ትምህርታዊ ጠቀሜታ ስለአለውና ብሔር/ብሔረሰቦች በራሳቸው ቋንቋ የመጠቀም መብታቸውን ስለሚያረጋግጥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትና ተመጣጣኝ ሥልጠና በብሔር/ብሔረሰብ ቋንቋ ይሰጣል፡፡

3.5.2. በሔር/ብሔረሰቦች አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረጉ በራሳቸው ቋንቋ ወይም በብሔራዊ ክልላዊና በሀገር አቀፍ ሥርጭታቸውና በተናጋሪ ብዛታቸው መሠረት በሚመርጡት ቋንቋ ሊማሩ ይችላሉ፡፡

3.5.3. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ግንኙነት የአማርኛ ቋንቋ በትምህርትነት ይሰጣል

3.5.4. የአፀደ ሕፃናትና የአንደኛ ደጃ መምህራንን ሥልጠና በአካባቢው ት/ቤቶች ለማስተማሪያነት የተመረጠው ቋንቋ የማሠልጠኛ ቋንቋ እንዲሆን ይደረጋል።

3.5.5. የእንግሊዝኛ ቋንቋ ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ እንደአንደ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል።

3.5.6. የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት በእንግሊዝኛ ይሰጣል።

3.5.7. ለባህላዊና ዓለም አቀፍ ግንኙነት እንዲያግዝ ተማሪዎች ከብሔር/ብሔረሰብ ቋንቋዎችና ከውጭ ቋንቋዎች መሀከል እንደፍላጎታቸው ቢያንስ አንድ የሀገር ውስጥ ቋንቋና አንድ የውጭ ቋንቋ መርጠው በተጨማሪ መማር የሚችሉበት ሁኔታ ይመቻቻል።

3.5.8. የቋንቋ ትምህርቶች በጥራትና በተጠናከረ ሁኔታ እንዲሰጡ ተገቢው ጥረት ይደረጋል።

## 3.6. የትምህርት የሥልጠና የምርምርና የልማት ተስተጋብሮት

3.6.1. የሙያና የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች በሙያቸው ተግባራዊ ብቃት እንዲኖራቸው በትምህርት ሂደት እንደአስፈላጊነቱ በልማትና በአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቤቶች የመስክ ልምድ እንዲያገኙ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

3.6.2. የትምህርት የሥልጠናና የምርምር ተቋማት ምሁራን በልማትና በአገልግሎት ሰጭ መሥሪያ ቤቶች እውቀታቸውን እያካፈሉ ልምድ የሚቀስሙበት እንዲሁም የልማትና የአገልግሎት ሰጭ መሥሪያ ቤቶች ባለሙያዎች ለትምህርት ተቋማት ልምድ የሚያካፍሉበት ቅንጅታዊ ሥርዓት ይመቻቻል።

3.6.3. በሥርዓተ ትምህርቱ አቀራረጽና አሰጣጥ በየዘርፉና በየደረጃው ከትምህርት ለሚለዩ ተማሪዎች በአጫጭር ሥልጠናዎች ሥራ ፈጣሪና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ የሚያስችል የተቀናጀ ይዘት መኖሩ ይረጋገጣል።

3.6.4. በጥናት ላይ በመመርኮዝ የመንግሥትና የግል ድርጅቶች ልማታቸውን ለማገዝ በየግላቸው እንደየአስፈላጊነቱ የሥልጠና ተቋማት እንዲያቋቁሙ ይደረጋል በመካከላቸውም ተስተጋብሮት መኖሩ ይረጋገጣል።

3.6.5. የትምህርት ደረጃ ተመጣጣኝነትን ለመጠበቅና የሥልጠና ድግግሞሽና ብኩንነት እንዳይኖር ለማድረግ የሥልጠና መርሐ ግብሮች ተመጣጣኝነትን ለብቃታቸው አስተማማኝነትና ለተማሪዎች ችሎታ ምሥክርነት ለማረጋገጥ ተገቢው አደረጃጀት ይፈጠራል።

3.6.6. መደበኛ ያልሆኑ ትምህርቶችና ልዩ ልዩ የሙያ ሥልጠናዎች በትምህርት ሚኒስቴር በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ተቋሞች ቅንጅታዊ አሠራር እንዲካሄድ ሥልት ይቀየሳል።

3.6.7. ባህላዊ ሙያዎች ከዘመናዊ ትምህርት ጋር እንዲቀናጁና እንዲዳብሩ ይደረጋል።

3.6.8. የምርምር ሥራ በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ላይ ተመሥርቶ በቅድሚያ በተግባራዊ ችግር ፈቺነት ላይ እንዲያተኩር የእውቀት አድማስን በማስፋት አዳዲስ ግኝቶች እንዲዳብሩ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

## 3.7. የትምህርት ድጋፍ ሰጪዎች /የትምህርት ማቀግወኛ ግብአቶች/

3.7.1. የትምህርቱን ጥራት በተገቢው ደረጃ ለማካሄድና የተማሪዎችን የአካል የአእምሮና የስሜት ጤናማ እድገት በሚጠብቅ ሁኔታ የትምህርት ቴክኖሎጂና ፋሲሊቲ በአእርከኑ ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ እንዲዘጋጅ ይደረጋል።

3.7.2. የትምህርት ቴክኖሎጂና ፋሲሊቲ ተገብውን ደረጃ ይዞ ተመጣጣኝንና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ በየእርከኑ እንዲቀርብና እንዲሠራጭ በተገቢ ሁኔታም ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

3.7.3. በሥርዓተ ትምህርቱ መሠረት እንደየትምህርት እርከኑ ባሕሪ ደረጃ ለመማር ማስተማሩ ሂደት መኀልበት ለምርምር ሥርጸትና አጠቃላይ ለልዩ ልዩ የትምህርት እንቅስቃሴዎች የትምህርት ቴክኖሎጂና ፋሲሊቲ አቅርቦት አበረጃጀትና አጠቃቀም በክልል በዞን በወረዳና በትምህርት ተቋሞች በግልግ በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶ በቅንጅት እንዲሠሩ ይደረጋል።

3.7.4. የትምህርት ድጋፍ ሰጪዎች አመራረት አጠቃቀም እንክብካቤና ጥበቃ ከዕቅድ እስከ አፈጻጸም በሕዝብ ተሳትፎ ይከናወናል።

3.7.5. በትምህርት ድጋፍ ሰጪዎች አመራረት አቅርቦትና ሥርጭት የግለሰቦችና የድርጅቶች ተሳትፎ እንዲጎለብት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

3.7.6. በትምህርት ድጋፍ ሰጪዎች ዝግጅት ሥርጭትና አጠቃቀም ለሴቶችና ትምህርት ተነፍገው ለቆዩ አካባቢዎች የተለየ እገዛ ይደረጋል።

3.7.7. የልዩ ትምህርት ተሳታፊዎች በትምህርት ድጋፍ ሰጪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ልዩ ድጋፍ ይሰጣል።

## 3.8. የትምህርት አደረጃጀትና አመራር

3.8.1. በሥራዎችና በሠራኞች መካከል ያለው ግንኙነት በሙያ ብቃት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ማድረግ እንዲሁም በሠራተኛና በኃላፊዎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት በጋራ ተሳትፎ ሂደት ሙያዊ እንዲሆንና መብት ግዴታና ኃላፊነት በግልጽ ታውቀው እንዲሠራባቸው ይደረጋል

3.8.2. የትምህርትና የሥልጠና ዘርፍ አበረጃጀት ያልተማከለ ቅንጅት ያለው ሆኖ የትምህርቱንና የሥልጠናውን ሥርጭት የሚያሰፋ የሚያበለጽግና ጥራቱንም የሚጠብቅ እንዲሆን ይደረጋል።

3.8.3. የትምህርት ተቋሞች ነፃ ውስጣዊ አስተዳደር ኖሯቸው እንደየትምህርት ተቋሙ ባሕሪና ተልዕኮ ከኅብረተሰቡ ከሚመለከታቸው የልማትና የምርምር ተቋሞች ከመምህራንና ከተማሪዎች በተውጣጡ ቦርዶች ወይም ኮሚቴዎች አማካይነት ዲሞክራሲያዊ አመራር እንዲኖራቸው ይደረጋል።

3.8.4. የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች አስተዳደርና ሥልጠና እንደሙያው ባሕሪ መራሔ ሙያንና የሥራ ሁኔታን አገናዝቦ መብትና ግዴታን አስጠብቆ ደመወዝን የሥራ ማነቃቂያንና የእድገት መሰላልን አስተካክሎ ይደራጃል።

## 3.9. የትምህርት ፋይናንስ

3.9.1. የመንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና ሥልጠና 10ኛ ክፍል እስከሚጠናቀቅ ባለው ያተኮረ ይሆናል ከዚያ በላይ ደረጃው እያደገ ሲሄድ የተጠቃሚው የወጭ አስተዋጽኦ እየጨመረ የሚሄድ ይሆናል።

3.9.2. አንፃራዊ ኋላቀር ለሆኑና ቀደም ሲል በቂ የትምህርት አገልግሎት ላላገኙ አካባቢዎች መንግሥት ልዩ የትምህርት ፋይናንስ ድጋፍ ይሰጣል። የተማሪዎች ተሳትፎ እንዲጨምር ማበረታቻዎችን ያዘጋጃል።

3.9.3. የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ እንዲጨምር መንግሥት በፋይናንስ ድጋፍ ያበረታታል፡፡

3.9.4. የላቀ ችሎታ ኖሮአቸው የመክፈል አቅም የሌላቸው ነፃ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3.9.5. መንግሥት የግል ባለሀብቶች በየደረጃው ት/ቤቶች እንዲከፍቱ ያበረታታል ሁኔታዎችን ያመቻቻል ልዩ ልዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

3.9.6. በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋሞች የውስጥ ገቢያቸውን በማዳበር ለትምህርቱ ሥራ ማጠናከሪያ እንዲያውሉት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

3.9.7. በየደረጃው ተፈላጊውን ክፍያ ተጠቃሚዎች በአገልግሎት ወይም ሠርተው የሚከፍሉበት ሥልት ይቀየሳል፡፡

4. ልዩ ትኩረትና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች

4.1. ሥርዓተ ትምህርቱን መለወጥና የሥርዓተ ትምህርት መሣሪያዎችን ማዘጋጀት

4.2. ለመምህራን ጉዳይ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ለውጥ ማድረግ

4.3. የትምህርት አደረጃጀት መለወጥ